የሚገባ ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ ተደረገለት ፡ ይልቁንም ፡ ከመቅደላ ፡ ይዞት ፡ የሄደው ፡ የጥንት ፡ መፃሪያና ፡ በብራና ፡ የተጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ ለሎንዶን ፡ ቢብልዮቴክና ፡ ለጥንታዊ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ የሚጠቅሙ ፡ በመሆናቸው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ተሰኙበት ። ስለዚህም ፡ ጄኔራል ፡ ናፒየርን ፡ «ባሮን ፡ ኦፍ ፡ መቅደላ» ፡ ብለው ፡ ሠየሙት ።



ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ራሳቸውን ፡ በሽጉጥ ፡ ገድለው ፡ እንደወደቁ ።

# የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

ስለ ፡ ጣሰው ፡ ጐበዜ ፡ ሞት ፡—ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጐበዜ ፡ እንደ ፡ ነገሡ ፡—ስለ ፡ ራስ ፡ አዳልና ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ።

ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የቀድሞ ፡ ስማቸው ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጐበዜ ፡ ነው ፡ አገራቸው ፡ ላስታ ፡ ዘራቸውም ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ ሲወርድ ፡ የመጣውን ፡ የነገሥታትን ፡ ዘር ፡ አሸንፈው ፡ በኀይል ፡ የነገሡት ፡ የዛጔ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ ይባላል ። አባታቸውም ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ ይባላሉ ።

ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጐበዜ ፡ በዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሕይወት ፡ መጨረሻ ፡ ከነበሩት ፡ መሳፍንት ፡ የበለጡና ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውም ፡ እስከ ፡ ፰ ፡ ሺሕ ፡ ይደርስ ፡ ነበር ። ይኸንኑም ፡ እንግሊዞች ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ፡ ወዳገራቸው ፡ በሚመለሱበት ፡ ቀን ፡ የመቅደላን ፡ ምሽግና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይምጡና ፡ እናስረክብዎ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ። ርሳቸውም ፡ መኳንንቶቻቸውን ፡ ሰብስበው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ብለው ፡ ቢያማክሯቸው ፡ አስሮ ፡ ይዞዎት ፡ ይሄዳልና ፡ አይሂዱ ፡ ብለው ፡ መጥፎ ፡ ምክር ፡ አቀረቡላቸው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ርሳቸው ፡ አልመጣም ፡ ስላሉ ፡ ላጎታቸው ፡ ለደጃች ፡ መሸሻ ፡ ምሽጉን ፡ ብቻ ፡ አስረከቧቸው ። ወዲያውም ፡ በመቅደላ ፡ ታስረው ፡ የነበሩት ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ እንግዴህ ፡ ገዢያችን ፡ እርስዎ ፡ ነዎት ፡ እያሉ ፡ ለዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጐበዜ ፡ አመኑላቸው ።

ከዚህም ፡ በፊት ፡ በደንቢያና ፡ በወልቃይት ፡ ጣሰው ፡ (ጥርሶ) ፡ ጐበዜ ፡ የሚባለው ፡ እንዲሁ ፡ ለመንገሥ ፡ ያስብ ፡ ነበርና ፡ ባ፲፰፻፷፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በ መጋቢት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ከበጌምድር ፡ በስተሰሜን ፡ በለሳ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ አድርገውት ፡ ጣሰው ፡ (ጥርስ) ፡ ጐበዜም ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞተ ።

ቀጥሎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለመንገሥ ፡ በጐጃምና ፡ በትግሬ ፡ በሸዋም ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ማስገበር ፡ የግድ ፡ ማስፈለጉን ፡ ተመልክተው ፡ መዠመሪያ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ጉዞ ፡ ዠመሩ ።

